# ከልክ በላይ ማክበር ካሿፊ ጋር ማበር (ከይገርማል) 05.11.2018

አንዳንድ ሰዎች ሰውን ለማስደሰት ተብለው የተፈጠሩ ናቸው ማለት ይቻላል። "ከእሱ/ከእሷ ጋር መዋል ዕድሜ ይቀጥላል፤ አሆሆ! ጥርስ እኮ አያስከድንም/አታስከድንም" የሚባልላቸው በብዙወች ዘንድ ተወዳጅነትን ያተረፉ ሰዎች አሉ። ተፈላጊና ተወዳጅ መሆን ደስ ይላል። አንዳንዱ ደግሞ "ነገር ጎርጓሪ፣ ቁስል ዘንቋሪ ይሆንና በደግ ሳይታይ "ኧረ እንዲያው ወዲያ!" እንደተባለ ያልፋል። እኔም ከእነዚህኞቹ ምድብ ውስጥ ሳልሆን አልቀርም። "ንግግርህ አይጥምም" የሚለኝ እንጅ "አበጀህ!" ብሎ የሚደግፈኝ ብዙም የለም። ለነገሩ እኔም ብሆን ሰውን ለማስደሰት ስል ብቻ ከሚስቁት ጋር በመሳቅ ከሚያለቅሱት ጋር በማልቀስ የኮሜዲ ሥራ መስራት አይሆንልኝም። አንድ ጊዜ የሆነውን ላጫውታችሁ። ከቤታችን የማትጠፋ አንድ ጎረቤታችን ነበረች። ሴትዮዋ ሥራ አልነበራትም። እና በመጣች ቁጥር ስለባለቤቷ ስታወራ እሰማታለሁ። እንደሚጠረጥራት፣ የቤት ወጭ አሟልቶ እንደማይሰጣት፣ አምሽቶ እንደሚመጣ፣ በቀና እንደማያነጋግራት፤ ሰርክ ይኸው ነው። ከሥራ ውየ ስገባ የእሷን እዬዬ መስማት ስልችት አለኝ። ባለቤቴ ጻጥ ብላ ታስጨርሳትና ይጠቅማል የምትለውን ምክር ትለግሳታለች። እኔ ግን እንዲህ ላለ ትግስት የታደልሁ አይደለሁም። አንድ ቀን ደክሞኝ ውየ ለማረፍ ወደቤቴ ስገባ ይህችው ሴት የተለመደው ብሶቷን ለባለቤቴ እየዘረዘረች ነበር። "እንዴት ነው አንች፣ እንዲህ ስታነሽው ስትጥይው ውለሽ ማታ አብረሽው ስትተኝ ምንም አይከብድሽም? ይጠረጥረኛል ምናምን ማለትሽስ ትክክል ነው? የእሱን ሀጢያት እየዞርሽ ከማውራት ይልቅ የሚያስጠረጥርሽን ነገር አለማድረግ አይሻልም? እንዲህ አፍ አውጥተሽ በየጎረቤቱ እየዞርሽ እንድትናገሪ ያደረገሽ የከፋ በደል ከደረሰብሽ ለምን አብረሽው ትኖሪያለሽ? ጥለሽው ሂጅ" አልኳት በሀይለቃል። ሴትዮዋ ቆሌዋ ተገፎ ሹክክ ብላ ስትወጣ ወ/ሮ ሚስት በነገር ጠመደችኝ። ያለችውን ብላ ስትጨርስ በማሳረጊያው "ጅልነትማ አለብህ፤ እንዴት ነው እንዲህ ነገር መዘርፈጥ" አለችኝ። ሴትዮዋ እንዲያ ከተናገርኋት በኋላ ብዙም ሳትቆይ ሁለት ልጆች አስታቅፋው በዚህ ወጣች በዚህ ገባች ሳትባል ጠፋች። ምንም ማድረግ አልችልም፤ እኔ እንዲህ ነኝ።

በኢትዮጵያ ታሪክ ገናና ስም ያላቸው እጅግ ብዙ ሴቶች እንደነበሩና አሁንም እንዳሉ ይታወቃል። በፖለቲካ፣ በማህበራዊ ጉዳዮችና በኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ከራስ አልፈው ለወገን ኩራት የሆኑ ሴቶቻችን ላቅ ባለ ሁኔታ ሊታወሱና ሊከበሩ ይገባል። ይህን የምናደርገው ባለውለታወቻችንን ለማሰብ ብቻ ሳይሆን ተተኪው ትውልድ እንዲማርባቸው ለማስቻልም ጭምር ነው። ልጆች ታላላቆችቻቸውን ለመምሰል የማያደርጉት ጥረት የለም። ገና ትንሽ እያሉ ወላጆቻቸው እና በዕድሜ የበላዮቻቸው የሚያደርጉትን ነገር ለማድረግ ሲጥሩ ይታያሉ። በዕቃ ዕቃ ጨዋታ ባልና ሚስት ሲባባሉ፣ ቡና እያፈሉ ሲጠራሩ፣ ሲገባበዙ፣ ያዩትን ማድረጋቸው ነው። የትልቅ ሰው ጫማ ማድረግና ልብስ መልበስ የትልቅነት ስሜት ይፈጥርባቸዋል። ምኞታቸው ትልቅ መሆን፣ ትልቅ ሆነው ሲደረግ ያዩትን ማድረግ፣ ዋና ተዋናይ መሆን ነው። በዚያ ዕድሜ የራስን የጉዞ መስመር ማስመር፣ ለየት ያለ ራዕይ ማመንጨት፣ የሚያስችል የዐዕምሮ ብስለት የሚኖር አይሆንም። ለዚያም ነው በቅርባቸው ያሉትን በዕድሜ የሚበልጧቸውን ሰዎች ፈለግ የሚከተሉት። እኛ ደግሞ ሰፋ ያለ አመለካከት ማዳበር እንዲችሉ በአቅራቢያቸው ከሚያዩት ባሻገር ተጉዘው እንደምሳሌ (Role model) ቢወስዷቸው ይበጃል የምንላቸውን ሰዎች ልናስተዋውቃቸው ይገባል። ራስን አሳልፎ ለሀገርና ለወገን መስጠትን፣ ለፍትህ እና ለዕኩልነት መቆምን፣ ሙስናን መዋጋትን፣ ለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር መታገልን፣ አላማን ከግብ ለማድረስ መጽናትን፣ ሊያስተምሩን የሚችሉትን ሰዎች የውሸት ሳይሆን የዕውነት ታሪክ እያፈላለግን ልናስተምራቸው ይገባል። ውሸት ሲገለጥ የወደፊት አመኔታን ያሳጣል። መዋሸት ውሸታምነትን እያበረታ ሀቀኝነትን ያዳክማል። ይህን እንድጽፍ ያነሳሳኝ ከሰሞኑ በየድረገጹ ስለብርቱካን ሚዴቅሳ የተጻፈው ጽሁፍ ነው። mereja.com ላይ

"ብረቷ እመቤት ብርቱካን ሚዴቅሳ መንግሥት ባደረገላቸው ጥሪ የፊታችን ረቡዕ ወደሀገራቸው ሊገቡ ነው" ይላል ጽሁፉ። "ከተናግሮ አናጋሪ ሰውረኝ!" ብየ ብጸልይም የሚሆን አልሆነም።

ከብርቱካን ጋር ጸብም ይሁን ፍቅር የለኝም። ግን በመጠኑም ቢሆን ስለርሷ አውቃለሁ። ብርቱካን በቅንጅት ወቅት ከነበሩት ሴት የሰላም ታጋዮች የበለጠ ያደረገችው አንድም ነገር አልነበረም። እንዲያውም ቅንጅት ባለፈባቸው ውጣ ውረዶች ላይም ተሳታፊ አልነበረችም። በቅንጅት አባላት ምልመላና አደረጃጀት ያስቀመጠችው የታሪክ አሻራ የለም። በምርጫ ቅስቀሳ አልተሳተፈችም። በምርጫ ክርክር ወቅት በመድረክ አልታየችም። እስከ 1997 ነሀሴ ድረስ በብዙወቹ ዘንድ ስሟም አይታወቅም ነበር። የብርቱካን ታሪክ ጎልቶ ይተረክ የያዘው እንዴት እንደሆነ ሳይታወቅ የቅንጅት ሁለተኛ ሰው ሆና ከኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ቀጥሎ ያለውን የሀላፊነት ቦታ ከያዘችበት ጊዜ ጀምሮ ነው። በድርጅቱ ውስጥ ምንም አይነት ድርሻ ማበርከት ቀርቶ አባል መሆኗ እንኳ ሳይታወቅ ነበር ወደስልጣን እንድትመጣ የተደረገው። ግን ለምን? በመኢአድም ሆነ በኢዴፓ ውስጥ አባላትን በመመልመል፣ በማደራጀት፣ በማንቃት፣ ድርጅታቸውን ለማጠናከር በገቢ ማሰባሰብ ሥራ በመሰማራት እና ያላቸውን በመለገስ ብዙ የሰሩ በትግል ተሞክሮም ሆነ በትምህርት ደረጃ ከእሷ የተሻሉ እያሉ ከየት መጣች ሳይባል እንዴት የቅንጅት ም/ሊቀመንበር ሆና ለመመረጥ በቃች? አንዳንድ ሰዎች በምክንያትነት የሚጠቅሱት ሚዛን የማይደፋ ነገር ተቀባይነት ያለው አይደለም። እነሱ የሚሉት አንድም ሴት በመሆኗ ሁለትም ከኦሮሞ ብሔረሰብ ስለተገኘች የሚል ነው። ይህ ግን ትክክል አይደለም። ምክንያቱም ነባር ሴት ኦሮሞ ታጋዮች በሁለቱም ድርጅቶች ውስጥ ስለነበሩ። ሌላው ምክንያት ደግሞ ዳኛ በነበረችበት ጊዜ የአቶ ስዬ አብርሃን የክስ መዝገብ መርምራ አቶ ስዬን ነጻ በመልቀቋ እንደጀግና በመታየቷ ነው የሚል ነው። ይህም ትክክል አይመስለኝም። በመጀመሪያ ደረጃ አቶ ስዬን በነጻ መልቀቅ እንደጀግንነት

ብንወስደው እንኳ ይኽ ምክንያት ለቅንጅት ተሿሚነት የሚያበቃት አይደለም። ቅንጅት አመራሩን ሊመርጥ የሚገባው በድርጅቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ብቃትና ተሳትፎ ገምግሞ እንጂ ከዚያ ውጪ በሆነ ጉዳይ ሊሆን አይችልም። በሁለተኛ ደረጃ ብርቱካን የአቶ ስዬን የክስ መዝገብ ስትይዝ በተከሳሹ ላይ እንድትፈርድባቸው ከወያኔ የተላለፈላት ትዕዛዝ ስለመኖሩም አልነገረችንም። ትዕዛዝ ተሰጥቷት ትዕዛዙን ተላልፋ ውሳኔ አሳልፋ ቢሆን እንኳ ሕጉ የሚለውን ተከትላ ውሳኔ በማሳለፏ በሙያ አክባሪነቷ እናደንቃት ካልሆነ በስተቀር የተለየ ክሬዲት የሚያሰጣት አይሆንም። ከሙያችን ስነምግባር ውጪ አንሰራም ብለው ከስራ የተባረሩ ዳኞች፣ ጋዜጠኞች፣ መምህራኖች፣ የጤና ባለሙያወች፣ የበረራ ሰራተኞች፣ ወታደሮች፣ - - - እጅግ ብዙ አሉ። እሷም ከእነዚህ እንደአንዱ ከመቆጠር ያለፈ ማዕረግ የሚያጎናጽፋት አይሆንም። በጥቅምት 1998 የተከሰተውን የሕዝብ አመጽ ተከትሎ ቃሊቲ ከታሰሩት የቅንጅት አመራሮች አንዷ የሆነችው ብርቱካን ከእስር ስትፈታ የጀግና አቀባበል ተደርጎላት ከአካባቢዋ ኗሪ ሕዝብ የመኪና ሽልማት ተበረከተላት። ሊያሸልማት የሚችል፣ ከሌሎች የሰላም ታጋዮች በተለየ መልኩ ያበረከተችው ጎልቶ የሚታይ ህዝባዊ አስተዋጽዖ አለ ወይስ የለም፤ የታሰረችበት ምክንያት አሳማኝ ነበር ወይስ አልነበረም፤ የተፈታችበት ሂደት ትክክል ነበር ወይስ አልነበረም፤ በመታሰሯ ምክንያት የተገኘ ጠቃሚ ነገር አለ ወይስ የለም የሚለው ጉዳይ ከግምት ሳይገባ ታስሮ መፈታቱ ብቻውን እንደጀግና አስቆጥሯታል። ቃሊቲ ከራርሞ መውጣት የሚያስከብርና የሚያሸልም ከሆነ ለምን የሌሎቹስ ስማቸው እንደርሷ ስም አልገነነም? ከእስር ቤት ከወጣች በኋላ ከነኢንጅነር ግዛቸው ጋር "አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ" የተሰኘ ፓርቲ መስርታ፣ የተፈተነ የአመራር ብቃት ስላላት ሳይሆን ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል ብቻ ሊቀመንበር ሆና እንድትመረጥ ተደረገ። ከዚህ ሁሉ በኋላ ስዊድን ሀገር ሄዳ የተናገረችውን ተከትሎ እንደገና ለእስር ተዳረገች። ከጥቂት ጊዚያት እስር በኋላ ያው እንደባለፈው ሁሉ እንደታምራት ላይኔ "ቢመክሩኝ አልሰማ ብየ" ምናምን አይነት ነገር ብላ ድጋሚ ይቅርታ ጠይቃ ለሁለተኛ ጊዜ ይቅርታ አግኝታ ተፈታች። ከዚያም ወደ አሜሪካ ሄዳ የግል ኑሮዋን ጀመረች። ታሪኳ ይኸው ነው። አንባቢ እንዲረዳልኝ የምፈልገው አንድ ቁምነገር አለ። ትንሽም ብትሆን በጎ ተግባር ያደረገን ሰው ውለታ መዘንጋት ትክክል እንዳማይሆን። በዚህም መሰረት ብርቱካን ላደረገቻቸው በጎ ነገሮች በሙሉ መከበር አለባት። ነገር ግን በጥሩ ሞዴልነት ልንወስዳት የምትገባ አይደለችም። "ብረቷ" የሚያሰኝ ተግባርም አልፈጸመችም። የማይመጥናትን ስምና ክብር መስጠት ከሹፈት ተለይቶ አይታይም።

ርዕዮት ዓለሙ ይቅርታ ጠይቂና እንፍታሽ ስትባል "ህቅ ካላወጣኝ ባልፈጸምሁት ጥፋት ይቅርታ ጠይቄ መውጣትን ዐዕምሮየ አይቀበለውም" ብላ ጽናትን አስተምራናለች። በዚህ ተግባሯ ርዕዮትን እንደሮል ሞዴል ብንወስዳት ትክክል ነው።

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም የወይዘሮ ሣህለወርቅ ዘውዴን የፕሬዚደንትነት ሹመት ተቃውመው በጻፉት ጽሁፍ "እኔን የሚገርመኝ የወ/ሮ ሣህለወርቅ መመረጥ አይደለም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ እልል ብሎ መቀበሉ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከታሪኩ የማይማር መሆኑ ነው። - - - የኢትዮጵያን ሕዝብ በቅንነት ያገለገለ ሰው ጠፍቶ? - - - አምላክ ዐዕምሯችንን ያብራልን" ሲሉ ይደመድማሉ፤ እኔም የምደግመው ይህንኑ የእሳቸውን አባባል ነው። በርግጥ ስለወ/ሮ ሣህለወርቅ በቂ ግንዛቤ ስለሌለኝ ስልጣኑ ይመጥናቸዋል ወይም አይመጥናቸውም ብየ ለመከራከር አልደፍርም። ፕሮፌሰር መስፍን ስለሚያውቋቸው ያሉትን ብለዋል። እኔ የወደድሁላቸው ስለብዙወቻችን ጭፍን ደጋፊነት የገለጹበት መንገድ ነው። ዕውነትን ሳይዙ በቲፎዞ የሚደገፍባት ሀገራችን በአድማ ስም የሚጎድፍባት ክብር የሚረክስባትም ናት።


እስተያየት

# የወይዘሮ ሣህለወርቅ ሹመት ትክክል አይደለም

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም

በመጀመሪያ እኔ ከወይዘሮ ሣህለወርቅ ጋር የወዳጅነትም ሆነ የጠብ ግንኙነት የለኝም፤ የምጽፈው ብችል የኢትዮጵያን ሕዝብ ለታሪክ ትዝብት ለማስመዝገብ ነው፤ ሌላ ዓላማ የለኝም፤ የሚቃወም ሰው ካለ፣ የምጽፈውን በማስረጃ ቢያስተባብል ይቅርታ ለመጠየቅ ዝግጁ ነኝ።

ወይዘሮ ሣህለወርቅ ለሦስት የኢትዮጵያ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዞች ቢታማኝነት ያገለገለች ሴት ነች፤ በውጭ ጉዳይ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ አገልግላለች፤ በውስጥ ጉዳይ አልገባችም የሚሉ አላወቂዎች ኢጋጥመውኛል፤ ለነዚህ መልስ መስጠት አስፈላጊ አይመስለኝም፤ ሆኖም አዲሱ አገዛዝ ወይዘሮ ሣህለ ወርቅ ለሦስቱ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዞች ያበረከተችውን አስተዋጽኦ ከባድ ሚዛን ውስጥ አስገብቶ የኢትዮጵያ መሪ እንድትሆን መርጧታል፤ ለእኔ ዋናው ነገር ወይዘሮ ሣህለ ወርቅ መመረጥ አይደለም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ እልል ብሎ መቀበሉ ነው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከታሪኩ የማይማር መሆኑን በግልጽ ያሳያል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ለኢትዮጵያ አገዛዞች ያላገለገለ ሰው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ ጠፍቶ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ በቅንነት ያገለገለ ሰው ጠፍቶ!.... ከቀበሯቸው መሀከል እያወጡ ሲጭኑብን እልል ካልን፣ ምን ቢጭኑብን እምቢ ልንል ነው? አምላክ አእምሮአችንን ያብራልን።

እውነት፣ ሚዛናዊነት፣ ፅናት፣ ህዝባዊነት

ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያምን "ዕውነት፣ ሚዛናዊነት፣ ጽናት ሕዝባዊነት!" ሲሉ መፈክር አሰምተው ጽሁፋቸውን ደምድመዋል። በመጨረሻም ማን አለብኝነትንና ሞፈር ዘመት አስተዳደርን በተመለከተ ዛሬም ትንሽ ማለት እፈልጋለሁ።

የትኛውም ማህበረሰብ ራሱን በራሱ እንዳያስተዳድር መከልከል ከምንም የበለጠ ከፍተኛው ጥቃት ነው። የሰው ልጅ ራሱ በሚመርጣቸው ሰዎች መመራት ካልቻለ የሚኖረው በባርነት ነው ማለት ይቻላል። በአንድ ከተማ ውስጥ በሚኖሩ አጎራባች ቀበሌዎች ውስጥ አንደኛው ቀበሌ ከሌላኛው ቀበሌ በተመረጠ ሰው እንዲተዳደር ቢደረግ የሚሰጠውን ትርጉም፣ የሚፈጥረውን

ስሜት፣ ዝም ብላችሁ አስቡት። ከሌላ ወረዳና ዞን ሰው ተሹሞ አንድን አካባቢ እንዲያስተዳድር ሲደረግ ደግሞ የሚፈጥረው ስሜትና የሚያስተላልፈው መልዕክት እጅግ የከፋ ይሆናል። እናንተ ለመተዳደር እንጂ ለማስተዳደር አልተፈጠራችሁም፤ አቅሙም የላችሁም በሚል ስሌት ከየትም እያመጡ በሕዝብ ላይ መሾም ከፊውዳሉ ሥርዓት ተሻግሮ እስካሁን የቀጠለ ሕዝብን የናቀ እጅግ አሳዛኝ ተግባር ነው። እንዲህ ያለውን ያፈጠጠ፣ ያገጠጠ ዕኩይ ተግባርን የማይቃወም ዜጋ ሙሉ ስብዕና አለኝ ብሎ ሊናገር አይችልም። ቢናገርም ገና ያልበሰለ ጥሬ፣ ለመብል እንጂ ለማሰብ ያልደረሰ ጉብል ከመሆን አይዘልም። የሕዝብን መብት እየረገጡ ሕዝባዊ መሆን አይቻልም፤ የሚደገፈውን መደገፍ፣ የሚነቀፈውን መንቀፍ ካልቻልን ዕውነትን ገድለን መቅበራችን እንደሆነ ማወቅ ይኖርብናል። መብታችንን ለማስከበር ግድ ካልሰጠን ዕውነትም ሿሚና ሻሪ ያስፈልገናል።

አድሏዊነትን እያወገዙ ማዳላት፣ ስለፍትህ እየጮሁ ፍትህ ማጉደል፣ ስለሰው ልጅ መብት እየተሟገቱ መብት ረጋጭ መሆን የሚያስተምረው አንድም ጥሩ ነገር አይኖርም፤ የመጨረሻ ውጤቱም አያምርም። አንድ ነገር ግን ልብ ልንል ይገባናል። የሚደርስብንን በደል መቃወም እስካልቻልን ድረስ ጥቃቱ ማቆም እንደማይችል። ስለዚህ መደራጀት ይኖርብናል። የምንደራጀው ራሳችንን ለመከላከል እና በደል ፈጽመውብናል ያልናቸውን ወገኖች ለመፋረድ እንጂ የማንንም ንጹህ ዜጋ መብት ለመጣስ መሆን የለበትም። ጥቃት ከቅርብም ከሩቅም ሊመጣ ይችላል። ትክክል ያልሆነ ነገር ከየትም ወገን ቢመጣ ትክክል ሊሆን ስለማይችል የትኛውንም ጥቃት መከላከል ተፈጥሯዊም፣ ህጋዊም መብት ተደርጎ መወሰድ አለበት።

ለትክክለኛ አላማ ተነሳስተን ነገር ግን አላማችንን ከዳር ለማድረስ የማንበቃ ከሆነ ጽናት ይጎድለናልና ባንጀምረው ይመረጣል በሚል ምክንያት ከትግል ማፈግፈግ አያስሄድም፤ እንደጀመርህ ጨርስ ለህዝባዊ ትግል ስለማይሰራ። አንዱ ሀሳብ ያመነጫል፤ ሌላው ሀሳቡን በተግባር ለመተርጎም ተንቀሳቅሶ የተወሰነ ርምጃ ይሄዳል፤ ቀጥሎ የሚመጣው ደግሞ ከባለፈው ትምህርት ወስዶ አሻሽሎ ያስቀጥለዋል፤ እንዲህ እንዲህ እያለ አንድ ቀን አላማ ከዳር ይደርሳል። ዋናው የተነሳንበት ነጥብ ዕውነትን መሰረት ያደረገ መሆኑ ላይ ነው። "ዕውነት ብትሰለስልም አትበጠስም" አይደል የሚባለው! ዛሬ ያልተገነዘቡ ቢኖሩ ነገ የሚመጡት እንደዛሬዎቹ እንደማይሆኑ መታወቅ አለበት። ዛሬ ጥለን የምናልፋቸው አሻራዎች ነገ ወይ ያስመሰግኑናል አሊያም ያስነቅፉናል።

አጼ ኃይለሥላሴ ስዩመ እግዚአብሄር ተብለው በስማቸው ይማልና ይፈከር ነበር። በደርግ ጊዜ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማሪያምን የሁለት ሰው ጭንቅላት ያላቸው ባለብሩህ ዐዕምሮ ባለቤት ሲባሉ እንደነበር እናስታውሳለን። በወያኔ ጊዜ ደግሞ አቶ መለስ ዜናዊ ባለራዕዩ መሪ፣ ዎርልድ ክላስ ማይንድ እየተባሉ ሲደነቁ ሰምተናል። "ጉድና ጅራት ወደኋላ ነው እንዲሉ ይኸው ዛሬ ሁሉንም በደግ ከሚያስታውሳቸው ይልቅ በመጥፎነታቸው የሚኮንናቸው ይበልጣል። ጉልበትና ስልጣን ባለን ጊዜ የምንፈጽማቸው የማንአለብኝነት ተግባሮች ቆይተው ከራስ አልፎ ለዘመድ አዝማድም ማፈሪያ ስለመሆናቸው አስረጅ ቢሆኑ ብየ ነው ሦስቱን ሰዎች በስም መጥቀሴ።

ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠቅም ተግባር ሳይሰሩ እንደልባቸው ለኖሩ እና በክፉ ድርጊታቸው ለሚታወቁ ሰዎች በቲፎዞ ኃይል ለመታሰቢያ ተብሎ በስማቸው የተሰየሙ መንገዶች፣ ድርጅቶች፣ ት/ቤቶች፣ መናፈሻወች በሙሉ በሀገር ባለውለታወች ስም እንዲቀየሩ መደረግ ይኖርበታል። አቶ መለስ፣ ጀኔራል ሀየሎም፣ አቶ ሙሏለም - - - የታገሉት ለኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያበረከቱት በጎ ነገርም የለም። ደርግን ቢታገሉ ደርግን ጥለው ሊነግሱብን ስለፈለጉ እንጂ ወደተሻለ አስተዳደር ሊያሸጋግሩን አልነበረም። ስለዚህ በሕወሀት እና በብአዴን ሰዎች የተሰየሙት ሁሉ በየአካባቢው ዕውነተኛ ጀግኖች ስም እንዲቀየሩ ግፊት ማድረግ ተገቢ ይሆናል። የትኛውንም ትክክል ያልሆነ ነገር መታገል ካልቻልን የሕዝብን የበላይነት ማረጋገጥ አይታሰብም። አምርረን በመታገል ለሕዝብ የሚታዘዝ መንግሥት መመስረት የሚያስችል ስርአት መገንባት ካቃተን ለህግ ሳይሆን እየተጠራሩ ለሚሿሿሙብን እብሪተኞች የምንታዘዝ ሕዝብ ሆነን እንቀጥላለን።

ለሁላችንም ልብ ይስጠን!